# ይድረስ ለመምህሩ !

ከመምህር ዘነበ በቀለ

መምህርነት ክቡር ነው። መምህር መሆን ከራስ ይልቅ ለሌላ ማሰብን፤ ከሚኖሩበት ዘመን በበለጠ ለሚቀጥለው ትውልድ መጨነቅን የሚጠይቅ ከባድ ሃላፊነት ያለበት ሙያ ነው። ስለዚህም ነው እንደማንኛውም ለጋ ወጣት ከወላጅ ከዘመዱ ጋር ሳይቀመጥ፤ ከድሎትና ከከተማ ህይወት ተለይቶ ሁሉንም ወዳጄ ወገኔ ብሎ በማያውቀው ሩቅ ስፍራ ለመኖር የሚያስወስነው። መምህርት በህይወቷ ውስጥ የምትደሰትበት ወቅት ቢኖር በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። ያም ቀን ያስተማረችው ተማሪ ትምህርቱን ጨርሶ ከክፍል ክፍል ሲሸጋገር ማየቱ ላይ ይሆናል። ይሁንና መምህራን ህይወታቸውን በሞላ ለሰው ሕይወት ሲሉ የሚኖሩ ናቸውና የራሳቸውን ህይወት ኖረው አያውቁም። ህይወታቸው በጉዞ ላይ ስለሆነች ቤት ንብረት የማበጀት ዕድላቸው እጅጉን የመነመነ ነው። "የሰው ህይወት ስከረክም እኔ ለኔ ኖሬ አላውቅም" እንዳለው ሎሬት ፀጋዬ፤ ከቆላ ወደ ደጋ እያለ መምህሩ የሚያሳልፋት የህይወት ዘመን ዘለአለም በጭንቀትና በመከራ ውስጥ የምትኖር ናት። ግዳጅና ዓላማው የሰው ልጅን ከድንቁርና አለም አውጥቶ የራሱ ጌታ ለማድረግ በመሆኑ፤ ከዚህ ዐላማ ጋር ተፃራሪ ሆነው ከሚቆሙ ጋር ሁሉ ፍልሚያ ውስጥ ስለሚገባ አርፎ የሚቀመጥበት ዘመን አይኖረውም።

መምህርን ሊያስከፋው ሊያሳዝነው የሚችለው ነገር ደግሞ የለፋበት የደከመበት ተግባር ሁሉ ፍሬ አጥቶ ህዝብ በበሽታ ሲቸገር በድንቁርና ቀንበር ስር ሲወድቅ ማየት ነው። ከቶውኑ! በዚህ በኩል እንደ ኢትዮጵያዊው መምህር ያልታደለ፤ ዕጹ አመድ አፋሽ የሆነ አለ ማለት አይቻልም። ምክንያቱም በ 66ቱ አብዮት ወቅት የማይናቅ ሚና የተጫወተው መምህር በግርግር ስልጣን ባገኘው የደርግ መንግስት ተጠቅቶ ከተማሪዎቹ ጋር እንደ ወንጀለኛ ተረሽኗል። በየፈፋው ተጥሏል። መምህር ገደልኩት አጠፋሁት ያለው ድንቁርና እንደገና አገርሽቶ ልክ እንደ ተስቦ በሽታ በሀገር ላይ ሲያንሰራፋ ተስተውሏል።

ኢትዮጵያዊ መምህር ሆይ! እነሆ! ችግርህን በተማሪዎችህ እውቀት አካክሰህና ታግሰህ ያሳለፈከው ነገር ተመልሶ ያንተ መጠቂያ ሊሆን በቅቷል። ተማሪዎችህ በጥይት፤ ህዝብህ በርሃብ ተጨርሰውብሃል። መተሳሰብ በጭካኔ ተተክቶ ስትመለከት፤ ዕድገት በሁዋላ ቀርነት ተለውጦ ስታይ፤ ልፋትህ ሁሉ መና እንደቀረ አውቀህ ቅስምህ እንዲሰበር ሆኗል። ያ! ያዘነ ልብህ የማገገሚያ ሰዓት እንኳ ሳያገኝ የጎሳ ሊቅ በሆነው በወያኔ መንግስት ጥቃቱ ጨምሮ እየተፈፀመብህ ነው። ኑሮህ ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ሆኖብሃል። በድጋሚ የበለጠ ወንጀል ተፈፀመብህ እንጂ! አልተስተካከለም። ከትዳርህ ከጊዜያዊው ቤትህ ንብረትህ ተፈናቀልክ እንጂ! እፎይ ብለህ እንድትኖር አልሆንክም። ያስተማርከው ህፃን በተማረው ትምህርቱ እንዳይሰራ ሲደረግ አስተዋልክ እንጂ! በስራ ፍሬህ ረክተህ አልኖርክም። ስለዚህም ልፋትህ ሁሉ ፍሬቢስ ሆኗል። የራስህ ልጅ በተወለደበት ስፍራ የራሱን አፍ መፍቻ ቋንቋ እንዳይማር ታግዷል። ያ! ጥንት የመምህርነት ሙያን ስትመርጥ የዘመርከው መዝሙርህ ሁሉ በጎጠኞች ምላስ ተክቸልችሏል። አዎ!

የገበሬው አባት፤
የዶክተሩ አባት፤
የመሃንዲሱ አባት፤
የወታደሩ አባት፤
መምህር አንተ ባትኖር መካን ነበር ህይወት፤
ብለህ ነበር። ያለ መምህር መማር ይቻላል ያሉ ዘመነኞች ቃልህን ተሳለቁበት።

አዎ! ጭንቅላት ይታረስ ዕውቀትን እንዝራ፤

ቴክኒዎሎጂ ጥበብ በእጃችን ይገራ!   /
በማለት ሀቁን ለማሳወቅ ጥረህ ነበር።

ሀገር በልማት አሸብርቃ እንድትታይ ለማድረግ። ልማቷ በራሷ ልጆች ጥረትና ትጋት እንጂ! ሊገዟቸው ባሰቡ ባዕዳን አፋዊ ድጋፍና የእጅ አዙር ተመላሽ ዳረጎት እንዳይሆን በማለት፤ ቀድመህ አስጠንቅቀህ ነበር። ስለዚህም ነው።

ውጡ ተራራውን አቋርጡ ሜዳውን፤
ሸንተረር እረሱ ዝሩ አዝመራውን
አጥኑ በፊደል ሀይል ቴክኒዎሎጂውን፤
ችግር ድንቁርናን አጥፉ በሽታውን።

በማለት ሀገር በቀሉን ዜጋ ልታሳስብ የመረጥከው። ታዲያ ምን ይሆናል። የለፋህበት ሁሉ እንዳይሆን ሆነ።ስለጠባብነት እንጂ! ስለ ሰፊዋ ኢትዮጵያ እንዳታስተምር ታገድክ። ለበርካታ ዓመታት ከለፋህበት ቀንሰህ ያጠራከምከውን የመምህራን ማህበር ጥሪትህን ተቀማህ። መሪዎችህ ከፊሉ ተገደሉብህ ከፊሉም ተሰደዱ። ሌሎችም ተንቀው ተዋርደው በጎሳ ጠቢባን ጥግ እንዲይዙ ተደረጉ። የመምህራን አለም አቀፋዊ ባህርይ፤ በክልልተኝነትና በመንደርተኝነት የጎጥ ስሜት እንዲለካ ታዘዝክ።

በአጠቃላይ የጉስቁልና ህይወት እንድትኖር ተፈረደብህ። አንተ መምህር በድንቁርና ላይ እንደፈረድክ ሁሉ፤ ድንቁርናም ጊዜ አግኝቶ በአንተ በመምህሩ ላይ እንዲፈርድ ሆኗል። በመሆኑም፤ ለዘመናት ስትታገለው የኖርከው ድንቁርና በሀገርህና በህዝብህ ላይ ነግሷል። ዛሬም እንደጥንቱ ጠመኔህን አንስተህ! ድንቁርናን አጥፋ! "ትመም በጎዳናው…" "አቁዋርጥ በሜዳው…" ብለህ መዘመርና ማዘመር የታሪክ ግዳጅህ ሆኗል። ስለዚህም መምህር ሆይ! ሀገርህ ህዝብህ በጉስቁልና ላይ ናቸውና፤ ስትዋጋው የነበርከው ግለኝነት ስሜት ያቆጠቆጠበት ዘመን ላይ ነህና፤ ዳግም የገበሬው አባት…. . የወታደሩ አባት ብለህ በመዝሙርህ ድንቁርናን ተዋጋ! ደንቆሮዎችን በዕውቀት አርጩሜህ ቅጣ! ንፁሃን ተማሪዎችህን ዳግመኛ ለሀገር ፍቅር አዘጋጅ። ከዚህ ወዲያ! በመምህርነት ሙያም ሆነ በመምህር ላይ ሊደርስ የሚችል ጥቃት አይኖርምና።

የመምህርነት ሙያ የተከበረ ይሆናል!!
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኖራለች!!

EthioLion.Com

EthioLion.Com